# የ2002 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**


1. መግቢያ ........................................................................................2
2. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም (CSRP) ..........................................3
3. ያልተማከለ የወረዳ አስ/እና የመልካም አስ/ፓኬጅ......................................5
4. ፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም (JSRP)...............................................6
5. የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም (Ecbp) ..........................................8

# 1. መግቢያ

የክልላችንን የማስፈጸም አቅም ችግር ከመሰረቱ ለመፍታት እና የአገልግሎት አሰጣጥን በማቀላጠፍ መልካም አስተዳደር የማስፈን ጉዳይ ቀጣይነት ባለው መልኩ ማረጋገጥ እንዲቻል ቁልፍና አበይት የትኩረት መስክ ለይቶ በማስቀመ□ የለውጥ ፕሮግራሞች □2002 በጀት ዓመት ዕቅ□ ተዘጋጅቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ የተለየው ቁልፍ የትኩረት መስክ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በአዳዲስ አሰራር፣ አደረጃጀትና በበቃ የሰው ሃብት ልማትና አመራር በመታገዝ /Organizational Transformation / እውን ማድረግና በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም በአንደኛ ሩብ አመት አፈጻጸምም በየደረጃው የሚታዩትን የማስፈጸም አቅም ችግሮች ደረጃ በደረጃ በመፍታት ተቋማት ሁለንተናዊ ለውጥ በማምጣት ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራር መዘርጋት እንዲችሉ ድጋፍ ተደርጓል፤ እየተደረገም ይገኛል፡፡ ያልተማከለ አስተዳደርን ማጠናከርና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመፍታት □ለዉጥ ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ እና ሁለተኛ ዙር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ያጠናቀቁ ሴክተሮችን ወደ ሙሉ ትግበራ በማስገባት ለውጡን ተቋማዊ መሰረት የማስያዝ ሥራዎችም ተከናውነዋል፤እየተከናወነም ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በስራ ሂደቱ እና በክልሉ የመሰረታዊ የስራ ሂደት አማካሪ ቲም በአንደኛ ሩብ አመት የተከናወኑ ተግባራት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2 የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም

ግብ 1፡- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በተሟላ ሁኔታ የተተገበረ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/

በሁሉም የመንግስት ተቋማት የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ በታቀደው መሰረት በአንደኛ ዙር የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ያጠናቀቁ 7 ሴክተሮች ሙሉ ትግበራ ያልተቋረጠ ምክርና የቴክኒካል ድጋፍ በመሥጠት በክልል ደረጃ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ በተ.ጋላና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በሁለተኛ ዙር ጥናት አካሄደው ሙከራ ትግበራ ሂደት ላይ የነበሩ ሴክተሮችን እና ስልሳ / 60 / የሥራ ሂደቶች ላይ ሙከራውን በትክክል አካሂዶ ስለማጠናቀቃቸው እና ለሙሉ ትግበራ ዝግጁ ስለመሆናቸው ግምገማ አድርጎ ግብዓት መስጠት እና ወደ ሙሉ ትግበራ ለማስገባት በታቀደው መሰረት .....የሥራ ሂደቶች ለ .... ፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን የአራት ሴክተር ታክስ አስተዳደር፣ማስታወቂያ፣ክልል ም/ቤት እና ርዕሰ መስተዳደር ያሉ የሥራ ሂደቶች የሙከራ ትግበራውን አጠናቀው የሰው ሃይል ድልድል በማከናወን ለፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት ወደ ሙሉ ትግበራ ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል በሁለተኛ ዙር ጥናት አካሄደው ነገር ግን የሙከራ ትግበራ ያላካሄዱ ተቋማት ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ገጠር መንገዶች ባለስልጣን፣ወንዶ ንግድ ኩባንያ፣ውሃ ስራዎች እና ብዙሃን መገናኛ ሲሆኑ በተለያዩ ምክንያት የሙከራ ትግበራ አፈፃፀም ያላካሄዱ እና ለመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ያልተዘጋጁ ናቸው፡፡

የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጡን ተቋማዊ መሰረት ለማስያዝ ትኩረት በመስጠት ከተከናወኑ ተግባራት ዋነኛው የሥራ ሂደትን መሰረት ያደረገ ተቋማት ማቋቋም ሲሆን ረቂቅ ተጠናቆና የማደበሪያ ሃሳቦች ታክለውበት በስቲሪንግ ኮሚቴ እና ካብኔ ቀርቦ

ጸደቋል፤ የአስፈጻሚ ተቋማት አደራጃጀት አዋጅ ተዘጋጅቶ ለክልል ምክር ቤት ለውሳኔ ቀርቧል፡፡የጋራ አገልግሎቶች አደረጃጀትን በሚመለከት በክልሉ የመሰረታዊ የስራ ሂደት አማካሪ ቲም ረቂቅ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

ግብ 2፡- በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ አሰራር

የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጡን ተቋማዊ መሰረት ለማስያዝና ተቋማዊ ለውጡን / Organizational Transformation / እውን ለማድረግ ውጤትን መሰረት ያደረገ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በአንደኛ ሩብ አመት የውጤት ተኮር ዕቅድ ማስፈጸሚያ ማኑዋል ለማዘጋጀት የታቀደ ቢሆኑም ከፌደራል ሥርዓቱን በወጥነት ባለው መልኩ ለመዘረጋት መፈጸም የሚገባቸው ሥራዎች ባለመከናወናቸው የማስፈጻሚያ ማኑዋሉን ማዘጋጀት አልተቻለም፡፡

ግብ 3፡- በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ሥራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሰራር

የአገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ብሎም ለተገልጋዮች በሚሰጠው አገልግሎት ተገልጋዮች ቅሬታ ካላቸው ቅሬታቸውን ሊያቀርቡ የሚቹሉበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በአንደኛ ሩብ አመት የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት የአሰራር ስርዓት መመሪያ በማዘጋጀት በመመሪያው ላይ ስልጠና ለመስጠት በታቀደው መሰረት ከርዕሰ መስተዳደር የቅሬት የስራ ሂደት ጋር በመቀናጀት ረቂቅ መመሪያው ተዘጋጅቷል፡፡

3. ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር ፕሮግራምና የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን በተመለከተ፡-

ግብ 4፡- በክልሉ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋና በተጠናከረ ሁኔታ ሥራ ላይ የዋለ አንድ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር

በክልሉ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓትን ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት የኢንስፔክሽን እና የሱፐርቪዥን አፈጻጸም ማኑዋል ረቂቅ ተዘጋጅቷል፤በዚህ ማኑዋል መሰረትም በየደረጃው ለሚገኘው ፈጻሚ አካላት እንዴት ኢንስፔክሽን ሥራ ማከናወን እንደሚቻል የስልጠና ሰነድ በቀጣይ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

ግብ 5፡- በሁሉም የክልሉ የቀበሌ መዋቅር አሣምኖ ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን በማስፋፋት ረገድ የተደረገ ድጋፍ

በአንደኛ ሩብ አመት ኀብረተሰቡን በግልና በጋራ ሥራ የማሣተፍና አሣምኖ ማሠራትን ባህል ለማዳበር ግልፅና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘረጋት እና የምርጥ ተሞክሮ መቀመሪያ ሰነድ ለማዘጋጀት በታቀደው መሰረት እያንዳንዱ ሴክተር ወጥነት ባለው መንገድ ምርጥ ተሞክሮዎቻቸውን በመቀመር ማስፋፋት እንዲችሉ የምርጥ ተሞክሮ መቀመሪያ ሰነድ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

ግብ 6፡- በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ

በቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ደረጃ የአሰራር ስርዓትን ለማጠናከር በታቀደው መሰረት የክልሉን የቀበሌ ስራ አስኪያጅ የአሰራር ስርዓት ማጠናከር የሚያስችል የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ስራአስኪያጅ በተሟላ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሠራ ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ በለቀቁ ስራ አስኪያጆች ምትክ የመተካት ሥራ እና አዲስ ቅጥር የተከናወነ ሲሆን በወረዳ ማዕከል ለሁሉም ቀበሌያት አዲስ ለተቀጠሩ ሥራ አስኪያጆች

ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሠራ ከማስቻል አኳያ በተመረጡ ቀበሌያት አራቱ የልማት ኮሚቴዎች በርግጥ መኖራቸውንና በቅንጅት እየሰሩ መሆናቸውን የማረጋገጥ እና የማጠናከሪያ ሥራ ተሰርቷል፡፡

ግብ 7፡- በሁሉም የአርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ተደርጎ የተተገበረ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ

የአርብቶ አደር አካባቢ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ በክልሉ ካብኔ ፀድቆ ለተሟላ ትግበራ የአፈጻጸም መርሐ-ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል በቅድሚያ ለአርብቶ አደር ዞንና ወረዳ አመራር ስልጠና ለመስጠት አስፈላጊው የሥልጠና ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

**4 የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም**

ግብ 8፡- በሁሉም የፍትህ ተቋማት የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር ተደራሽ፣ ወጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል

በክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ስኬታማነትና ውጤታማ ለማድረግ የፍትህ አካላትን በስልጠና ለማብቃትና ተkማቱን በሰው ሃይልና በማቴሪያል ለመደገፍ በታቀደው መሰረት ከአርብቶ አደር አካባቢ ተመልምሎ በመደበኛ ፕሮግራም የህግ ትምህርት ለሚያጠኑ 100 ዲፕሎማ ተማሪዎች ከዛየን ቴክኖሎጂና ቢዝነስ ኮሌጅ ጋር ውል ስምምነት በመፈጸም ከሃምሌ ወር ጀምሮ ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የፍትህ ተቋማትን ቀልጣፋ፣ውጤታማ እና ተደራሽ ለማድረግ በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት የአቤቱታ መመርመርና ዉሳኔ መስጠት የሥራ ሂደት ከሙከራ ወደ ሙሉ ትግበራ በማሸጋገር የፍትህ አሰጣጡ ተደራሽ፤ ወጪ ቆጣቢና ጥራት ያለው እንዲሆን አስችሎታል፡፡

- **የፍትህ አካላት የሥልጣን ማዕከል**

- በሩብ ዓመት መጀመሪያ ላይ ለመጀመሪያ ዙር ተቋሙ ያሰለጠናቸውን ሰልጣኞች በማስመረቅ እና የሥራ መመሪያ በመስጠት ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል ፣
- በክልሉ የህግ ጥናትና ምርምር በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ከሐዋሳ ዩኒቨርስቲ የህግ ፋካሊቲ ጋር በቅንጅት መስራት በሚቻልበት አግባብ ላይ ስምምነት ተፈራርሟል
- በ2ኛ ዙር በመሰልጠን ያሉ በአቃቤ ህግ ያለውን የመስክ ሥራ አጠናቅቀው ወደ ዳኝነት የመስክ ሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡በዚህም ተቋሙ የመስክ ግምገማ በማድረግ ግብረ መልስ ሠልጣኞች እንዲያገኙ አድርጓል፣
- በዩኒሴፍ Sponsorship 15 ዐቃቤ ህግና 15 ዳኞች በህጻናት ፍትህ ለ10 ቀን ሥልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፣
- ለሦስተኛ ዙር ሥልጠና ህዳር 1/2002 ለማስጀመር በዲግሪ 110፣ በዲፐሎማ 50 ተመልምለው ለማሰልጠን ዝግጅቱ ተጠናቋል፣

**በፖሊስ ኮሚሽን**

- በክልሉ በሥራ ላይ ላሉት ፖሊሶች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለ686 ለመደበኛ ፖሊስና ለ199 የማረሚያ ፖሊስ አባላት በመስከረም 30/2002 የአጭር ጊዜ ሥልጠና ተሰጥቷል፣
- የልዩ ኃይል ሥልጠና በክልሉ ፖሊስ ኮሌጅ ለ644 የፖሊስ አባላት የ3 ወር ሥልጠና በዚህ ወር መጨረሻ የሚጠናቀቅ ይሆናል፣
- በኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ኦፊሰርነት በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ ዲፕሎማና ከዚህ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸውን ከክልላችን 183 ፣ ከጋምቤላ ክልል 20 የፖሊስ ክፍተት ለመሙላት በፖሊሲ ኮሌጅ ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡
- አጠቃላይ የክልሉን ነባር የፖሊስ አባላት አቅማቸውን ለማሳደግ በተለያዩ የሥልጠና መስክ 6000 አባላት ለማሰልጠን ከታቀደው 2820 ነባር የፖሊስ አባላትና የፖሊስ አመራር በተለያዩ የማሠልጠኛ ተቋማት ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

ግብ 9፦ በሁሉም ቀበሌያት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ የተደረገ ድጋፍና ክትትል

በሁሉም በክልሉ የገጠር እና የከተማ ቀበሌያት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ስርዓት በተጠናከረ መልኩ ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት

- የኮሙኒቲ ፖሊሲንግን አሠራር ከመዘርጋት አኳያ ከፍትህ ተቋማትና ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት በዞን ደረጃ ውይይት ተካሂዶ አቅጣጫ ተይዟል፣ሥርዓቱንም ለማጠናከር በሁሉም ዞን ማዕከል ቼክሊስት በማዘጋጀት ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡
- በወላይታ ዞን ስር ላሉ ለሁሉም ወረዳዎች በሰንቴሪያ /ኮሙኒቲ ፖሊሲንግ/ ወንጀል መከላከል ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በጋሞ ጎፋ ዞን የኮሙኒቲ ፖሊሲንግን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በዞን ደረጃ ማስፈጸሚ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለሁሉም ወረዳና ቀበሌ ተሰራጭቷል
- በአዋሳ ከተማ አስተዳደር ከስምንቱ ክፍለ ከተማ ለተወጣጡ፡-
  - የፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊዎች
  - የኮሚኒቲ - ሊሲንግ ኦፊሰሮች
  - ዋና አስተዳዳሪዎች
  - የፍትህና ፀጥታ ኃላፊዎች
  - የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች
  - የፖሊስ መምሪያ ኃላፊ
  - የወንጀል መከላከል የሥራ ሂደት ኃላፊዎች ጋር በጋራ በኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ዙሪያ ውይይት በማድረግ ስራውን ለማጠናከር በስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

## 6. □ምህን□ስና አቅም □ንባ□ □ሮ□ራም

ግብ 10፡- በምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም የመንግስትና የግሉን ሴክተር ለማጠናከር አራት ጊዜ የተደረገ ድጋፍና ክትትል

### ➢ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት በተመለከተ

ኘሮግራሙ የሪፎርም ኘሮግራም እንደመሆኑ መጠን በሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚተገበር ኘሮግራም ሲሆን በዚሁ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር በ2002ዓ.ም ዕቅዳቸው ውስጥ አካተው መተግበር እንዲችሉ ለማድረግ በተደረገው ጥረት ከግብርና ገጠር ልማት ቢሮ፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፣ ከቴ/ሙ/ት/ሥ/ተቋም ውስጥ ከሚመለከታቸው የሥራ ሂደቶች

እቅድ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም ሁለተኛው የስትሪንግ ኮሚቴ ስብሰባ ያካሄደ ሲሆን ኘሮግራሙም በየባለድርሻ አካላት በበጀት የተደገፈ ሥራ እየተሰራ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሰራ እንደሚገባውም መተማመን ላይ ተደርሷል፡፡ የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም በየደረጃ ላለው ለዞን፣ለወረዳ እና ለከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ስለ ፕሮግራሙ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚረዳ የአሰራር ማኑዋል / working manual / በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

## ➢ የጥርብ ድንጋይ ንጣፍ / coble stone / ሥራን በተመለከተ

የጥርብ ድንጋይ ንጣፍ ሥራን በተመለከተ በክልሉ በሚገኙ 22 የሪፎርም ከተሞች ሥራውን መስራት እንዲችሉ የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከእያንዳንዱ ከተማ አስተዳደር ሁለት ሁለት አባላት እንዲሳተፉ ሲደረግ በአጠቃላይ ሶስት ቦታ በሐዋሣ፣ ሶደና ወልቂጤ ከተሞች ስልጠናው የተሰጠ ሲሆን የሥልጠናውም ትኩረት የዕቅድ አወጣጥና ሥራውን ለመምራት የሚያስችል ስልጠና ሆኖ በውጪ ባለሙያዎች በስፋት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

በክልሉ ከሚገኙ 22 የሪፎርም ከተሞች በ21 ከተሞች በ2002ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅዳቸው ውስጥ እንዲካተት ሆኗል፡፡

በሐዋሳ ከተማ 32000ካ.ሜ መንገድ የተሰራ ሲሆን 2332 ሥራ አጥ ወገኖች የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ሲሆን እንዲሁም በዲላ ከተማ 2500ካ.ሜ መንገድ የተሠራ ሲሆን 1853 ሠራተኞችን አሳትፏል፣ ሶዶ ከተማ 2800ካ.ሜ መንገድ የተሰራ ሲሆን 1252 ሠራተኞች አርባምንጭ 1300ካ.ሜ መንገድ የተሰራ ሲሆን 745 ጉልበት ሠራተኞች በሥራው ተሣትፈዋል፡፡ በአላባ ከተማ 1200ካ.ሜ መንገድ የተሠራ ሲሆን 412 የሰው ኃይል የተሣተፈ ሲሆን ሆሳዕና 800 ካ.ሜ መንገድ የተሰራ ሲሆን የጉልበት ሠራተኞች 115 የሰው ኃይል ተሣትፈዋል፡፡

## ➢ እሴት ሰንሰለት / Value chain / በተመለከተ

የቆዳና ሌጦ ጥራትን በተመለከተ ከፌዴራል የምህንድስና አቅም ግንባታ የዘርፉ ባለሙያና ከግብርናና ገጠር ልማት በፌዴራል ምርምር ኢንስቲቲውት የተገኙ ባለሙያዎች በዘርፉ ያለውን ችግር በመግለፅ ከፍተኛ ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑንና የክልሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ተገቢው በጀት እንዲመድብለት ውይይት ተደርጎበታል፡፡

በግል ተቋማት ዙሪያ የሚሰሩት የእሴት ሠንሰለት ሥራ አጠናክሮ ለመቀጠል እንዲቻል አንድ ባለሙያ በቀርከሃ ልማትና ምርት ጥራት ላይ ለመሥራት የተላከው ባለሙያ በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ መሥራት እንዲቻል ቢሮና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ ማግኘት እንዲችል ተደርጓል፡፡

በዝንጅብል ምርት የተሰማሩ ባለሃብቶች በአካባቢው በመሬት አቅርቦት ዙሪያ ተፈጥሮ የነበረው አለመግባባት ከክልሉ ኢንቨርስትመንት ጋር በመሆን ችግሩ የሚቃለልበት ሁኔታ እንዲመቻች ተደርጓል፡፡

## ➢ የቴክኒክ ሙያ ስልጠናና የቦርድ እንቅስቃሴ በተመለከተ

በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋም የመምህራን ብቃት ማረጋገጫ ምዘናንና ሥልጠናን በተመለከተ 135 ነባር መምህራንና 61 አዲስ ተቀጣሪ መምህራን በጠቅላላው 196 በደረጃ “C” በአዳማ የሥነ መምህራንነት ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ለ71 የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋም መምህራን ለሦስት ሣምንታት በተለያዩ የሙያ መስኮች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በክልል ደረጃ የተቋቋመው ካውንስልና በየተቋማቱ ለተቋቋሙት ቦርድ አካላት መተዳደሪያ ደንቦች ተዘጋጅተው ተሠራጭተዋል፡፡

- የካውንስልና የቦርድ አባላት በሠነድ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል
- የክልሉ የልህቀት ማዕከል /COC/ አጠቃላይ ገጽታውንና አሠራሩን በተመለከተ በክልሉ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በ12 ከተሞች የሚገኙ 40 የሚሆኑ መስሪያ ቤቶችና ባለድርሻ አካላትን የሸፈነ የማስተዋወቅ ብሮሸር የማደልና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተከናውኗል
- ሥርዓተ ትምህርት ላልተዘጋጀላቸው ሙያዎች ስርዓተ ትምህርት ማዘጋጀትና TTLM ተዘጋጅቷል
- የቀርከሃ ሥራ የሙያ ደረጃ ምደባ በመከናወን ላይ ይገኛል
- የበርበሬና የእንስት ውጤቶች በዘመናዊ መንገድ የማቀነባበር ሥራዎች የሙያ ደረጃ ምደባ ለማውጣት በአንድ ክላስተር ውስጥ ቅድሚያ ተሰጥቶት በጅምር ይገኛል
- ዳቦና እንጀራ ጋገራ፣ ደረቅ ምግብ ዝግጅት ፀጉር ሥራና ውበት እንዲሁም እፅዋትና እንሰሳት ተረፈ ምርት በአካባቢ ሙያነት ተለይተዋል፡፡
- የቆጮ መፋቂያ በሀዋሣ ቴ/ሙ/ት/ሥ/ኮሌጅ ተሠርቶ ተጠናቅቋል
- ሁለት የመንግስት የቴ/ማ/ት/ሥ/ተቋማት የመጀመሪያ ዙር ምልከታ ተደርጎ ለምዘና ጣቢያነት የማያበቃ ተጨማሪ ሥራ እንዲያጠናቅቁ ምክርና ድጋፍ ተሠጥቷቸዋል

- በኮንስትራክሽን ፣ በኢንዱስትሪያል ፣ በቢዝነስ አገልግሎት እና በሆቴል ቱሪዝም የሙያ መስኮች በ30 የሙያ ዓይነቶች ተመዝጋቢዎች ተጋብዘው 620 ሙያ ብቃት ተመዝጋቢዎች ለምዘና ዝግጁ ተደርገዋል
- ከ20 የመንግስት ቴ/ሙ/ት/ሥ/ተቋማት ከ300 በላይ የሆኑ የB-level መምህራን ለመመዘን የሚፈልጉበትን ሙያ እንዲመርጡ ተደርጎ መረጃው ተጠናቅሯል
- ለ100000 ሥራ አጥ ወጣቶችና ማህበር በማደራጀት በተለያዩ ሙያዎች የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ለመስጠት ከክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር የስምምነት ውል በመፈራረም ስልጠናውን በየተቋማቱ ለመጀመር ዝግጅት ተደርጓል
- የሀዋሣ ቴ/ሙ/ት/ሥ/ኮሌጅ የISO ሰርተፊኬት ለማግኘት ከሚሠራው ሥራ አንፃር ለድጋፍ ሠጪ ሰራተኞች በ “Procedures Work Instructions” እንዲሁም ሪከርድና ዶክመንት አያያዝና ልዩ ልዩ ቅፃቅጾች አጠቃቀም ላይ ስልጠና የማስተባበር ሥራ ተሠርቷል
- በተለያዩ ሙያዎች ተጀምሮ የነበረው የትብብር ሥልጠና ሲከታተሉ የነበሩ 683 ሠልጣኞች በየሩብ ዓመቱ ሥልጠናውን አጠናቅቀዋል፡፡

## ያጋጠሙ ችግሮች

- በምንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም በአንዳንድ ከተሞች የመረጃ አያያዛቸው ልውውጥ አለመጠናከር
- የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በተጋጋለ ስሜት ተግባራዊ ለማድረግና ዳያመንዱን ለማሟላት የሚደረጉ ጥናቶችና አዳዲስ አሰራሮች ከፌደራል አለመውረድ

## የተሰጡ መፍትሔ ሃሣቦች

- በቀጣይነት ያልተቋረጠ ግንኙነት ስርዓት መዘርጋት በስልክና በፋክስ በሚደረግ ግንኙነት የአሠራር ክፍተት እንዳይፈጠር በማድረግ መረጃዎችን መለዋወጥ
- ከፌደራል ዳያመንዱን ለማሟላት የሚደረጉ ጥናቶችና አዳዲስ አሰራሮች በፍጥነት ተግባራዊ የሚሆኑበትን አግባበ ከአቅም ግንባታ ሚ/ር ጋር ስምምነት ላይ መድረስ